

**<u>መምጣት</u>** **<u>Integration</u>**

**<u>መሄድ</u>** **<u>Deintegration</u>**

**<u>መመለስ</u>** **<u>Reintegration</u>**

*ዳደ ደስታ dadeyom@gmail.com*

## *1. የሁለት ባንዴሮች ወግ*

ከጥቂት ሳምንታት በፊት ኢጋድ ሸራተን አዲስ ውስጥ አንድ አነስተኛ ስብሰባ ጠርቶ ነበር። ያው የደቡብ ሱዳን ጉዳይ ነው። መቸም አሁን የኢጋድ ተልዕኮና ሥራ በደቡብ ሱዳን ወቅታዊ ሁኔታ ልክ የጠበበ ሆኗል። የኢጋድ ጣልቃ መግባት የሚጠይቅ ሌላ ተጨማሪ ጉዳይ ጠፍቶ ግን አይደለም። ዓረቦችና ወሃቢስቶች ቀይ ባህርን በሁለቱ ዳርቻ ሳንዲዊች አድረገው ከበውታል። የመሃል ዳኝነቱንም አራጋቢነቱንም ግጥም አድርገው ዘግተው ሲቆጣጠሩ ኢጋድ ኮሽታ አላሰማም። የመንን ከአፍሪካ ቀንድ ዕይታ ጋርደው የግል ጓሮአቸው ይመስል የGCC አገሮች ለብቻቸው ሲፈነጩበት፣ ኢጋድ እጅ ብቻ አይደለም ያጠረው፣ ድምጽ ጭምር እንጂ። የኤርትራውያን ፍልሰትና መከራስ ቢሆን? የሩቅ አገር ሰዎች፣ አውሮፓውያንና ዓለማቀፍ ድርጅቶች ጉዳያችን ብለው ሲንጫጩበት ኢጋድ በገዛ ህዝቡ ላይ ባይተዋር ይሁን?!

አገር ሙሉ እየፈለሰ በጉዳዩ ላይ ኢጋድ አንድ የምክክር ስብሰባ እንኳ አለመጥራቱ ክፋት ባይባል ክፍተት ነው።

ኤርትራ ወደ ኢጋድ አባልነቷ የመመለሷ ነገር የተራዘመ ሂደት ላይ ያለ ይመስላል። ወይም ሁነኛ መረጃ የለንም። በግልጽ እሚታወቀው ራሷን ከኢጋድ እንዳገለለች፣ ጥቂት ዓመታት ቆይታ ደግሞ መመለስ ፈልጋ ጥያቄ እንዳቀረበች፣ የኢጋድ በር ስታንኳኳ ለጊዜው የሚከፍት እንደጠፋ ነበር። እስካሁን ማንኳኳቷ ትቀጥል፣ ትታው ትቀመጥ፣ በሩ ይከፈት ወይም በመከፈትና ባለመከፈት መሃል ገርበብ ይበል፣ እርግጡን አልሰማንም። ሁኔታው ግን ሁሌም መመለስ እንደ መውጣት የቀለለ አለመሆኑ ማሳያ ይሆናል።

ወደ ሸራተኑ ስንመለስ፣ በዚህኛው የኢጋድ ስብሰባ ላይ አንድ ቀልብ የሚስብ ሁኔታ አየን። የሁሉም የኢጋድ አባል አገራት፣ ኤርትራን ጨምሮ፣ የ8ቱንም አባል አገራት ባንዴሮች ባማረ ሁኔታ እኩል ከፍታ ላይ ጎንለጎን ተደርድረው ይታያሉ። የኢትዮጵያና የኤርትራ ባንዴሮች ደግሞ ኩታገጠም ነበር የተሰቀሉት። መሰቀላቸው ብቻ ሳይሆን ተነካክተው/ተደጋግፈው ነበር። በበጎ ምኞት ለሚያያቸው አፍላፍ ገጥመው ሚስጥር የሚያንሾካሽኩ ይመስላሉ። በመካከላቸው ንፋስም ወንዝም አልነበረም።

ያ ሁሉ ጸብና ጦርነት በነሱ ስም መካሄዱ አያውቁም፣ አለዚያም እሱን በሌላ ማስረሻና ማርከሻ ቀድሰውታል። አብረው መውለብለባቸው ድምቀት ጨመረላቸው እንጂ ህልውናቸውን አልቀነሰም። መገፋፋቱ ድሮም ከሰው እንጂ ከባንዴሮቹ አልነበረም።

## *2. ኢሳያስ ሰጠ፣ ኢሳያስ ነሳ - ዜግነትም ቢሆን*

የኢጋድ አገራትን ባንዴሮች ወክለው ወደ ስብሰባው የመጡ ሰዎችም ነበሩ። ያለተወካይ ዜጋ የተገኘችው አንዷ ብቻ ናት - የኤርትሯ። ርግጥ አምባሳደር ሃይሌ መርቆርዮስ በቦታው ነበሩ። ይሁንና አምባሳደር ሃይሌ እና የኤርትሯ ባንዴራ አንድ መድረክ ተጋሩ እንጂ ሁለቱም አይወካከሉም። እኝህ ሰው ከዚህ በፊት ይህችን የኤርትራ ባንዴራ ወክለው ኢትዮጵያ ውስጥ ኖረውም ሰርተውም ያውቃሉ። አሁን ግን የሥራ ውክልናቸው ለተባበሩት መንግስታት፣ የዜግነት ውክልናቸው ደግሞ ለደቡብ አፍሪካ ሆኗል።

አምባሳደር ሃይሌ መርቆርዮስ የኤርትራ ዜግነታቸውን በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት ተነጥቀዋል። እንዲያውም እሳቸው አጋጣሚው ውጭ ስላቆያቸው በዚህ ተገላገሉት እንጂ ቡድን-15 በሚባል የሚታወቁት አምሳያ አቋም የነበራቸው ጓደኞቻቸው ስውር እስር (incommunicado) እንደገቡ ዛሬ ድረስ እጣ-ፈንታ-ፍጻሜያቸው ሳይታወቅ 15 ዓመታት ደፈነ። ሰዎቹ የታሰሩት በፈረንጅ መስከረም 2001 የኒውዮርክ ሰማይ-ጠቀስ ግዙፍ መንታ ፎቆች በአሸባሪዎች ተመተው በፈረሱ ማግስት ነበር። ያ ቦታ ፍርስራሹ ተነስቶ ያማሩ ተተኪ ህንጻዎች ቆመውበታል። እነ ጴጥሮስ ሰለሙን ግን ያፈረሱት ህንጻ ሳይኖር ከፍርድና ከዘመድ እይታ ውጭ ይማቅቃሉ።

ዘንድሮ 25ኛ የነጻነት በዓላቸውን እያከበሩ ያሉት ኤርትራውያን ይህን ድርጊት በምን ሚዛን ያዩታል?

አገር ውስጥ ያለው የኤርትራ ህዝብ ቁጥር ከ3 ሚልዮን አይበልጥም። በ1997 አጠቃላይ የኤርትራ ህዝብ ቆጠራ (ሴንሰስ) ተካሂዶ ነበር። የጠቅላላው ህዝብ ቁጥር 2.6[1] ሚልዮን እንደነበረ አስተማማኝ የሚመስል መረጃ አለ። አቶ ገብሩ አስራት ባሳተሙት መጽሃፍም ከጦርነት ቀደም ብሎ የህዝባዊ ግንባር ሊቀመንበር የነበረ ሮመዳን መሓመድ ኑር የኤርትራ ህዝብ ቁጥርን አስመልክቶ ተቀራራቢ አሃዝ እንደነገራቸው ይጠቅሳሉ። የቤት ወይም የቤተሰብ ቁጥር ደግሞ አንድ ሚልዮን አይደርስም ወይም በትክክል በ1997ቱ (እንደፈረንጆቹ) ቆጠራ 650ሺ ይሆናሉ። ከቆጠራው በኋላም የአቶ ኢሳያስ መንግስት ብዙ ቤቶችና ቤተሰቦች አፍርሷል። ለ2001 ጥናታዊ ትንበያ (projection) ተደርጎ የተገኘው ቁጥር 2.9 ሚልዮን የሚል ነው። የህዝብ ቆጠራው አሁን ቢደረግ ከዚያ ወዲህ ጦርነቱ፣ ተፈጥሯዊ ሞቱና ፍልሰቱ ይበልጥ ቀንሰውት ይሆን እንደሆነ እንጂ መዋለዱ ከመጓደሉ በላይ ሚዛን ደፍቶ አጠቃላይ ቁጥሩ ይጨምራል ተብሎ አይገመትም።

የአሁኑ ስደት ክርስትያኑና ደገኛው ላይ ይበረታል።

የኤርትራ ህዝብ የደረሰበት መከራ ሲታሰብ የአሁኑ ስደት ብቻ ሳይሆን ድሮ ከኤርትራ ነጻነት በፊት ተሰደው በሱዳን ስደተኛ ካምፕች ላይ ያሉና አገራቸው ነጻ ሆናለች ከተባለ በኋላ መመለስ ያልቻሉትንም ማሰብ ያስፈልጋል። አርቀው ያልተሰደዱት አንድ ቀን አገራችን እንመለሳለን በሚል ተስፋ ይመስለኛል። ስለዚህ ያልተመለሱት ስላልፈለጉ ሳይሆን ስላልተፈቀደላቸው ነው። እነዚህ በመቶዎች ሺዎች የሚቆጠሩ ስደቶኞች አብዛኞቹ ከቆላው አካባቢ የሄዱና ከ40-50 ዓመታት በላይ ተሰደው የቆዩ ናቸው። እነዚህኛዎቹ ያሉባቸው ካምፖች አሁን ቢጎበኙ፣ ከመጀመርያዎቹ ስደተኞች ይልቅ ስደት ላይ ተወልደው ያደጉና ኤርትራን የማያውቋት ይበዛሉ።

የህዝብ ቁጥርና ስደት በተመለከተ እነዚህን መረጃዎች መጥቀስ ያስፈለገው ኤርትራ ምን ያህል አነስተኛውን የህዝቧን ቁጥር በስደት ፍልሰትና መደበኛ የቤተሰብ ምስረታ ዕድል በማጣት ምክንያት 'ከብዙ ተባዙ' ይልቅ ወደ 'ጥፉ ተበታተኑ' (depopulation) እንደተሸጋገረ ለማመልከት ነው። ከዚያም በአሁኑ ጊዜ ጥቃቱና ፍልሰቱ

በደገኛው ላይ አይሎ በመከሰቱ ምክንያት ሚዛኑ የተዛባ ውቅረ-ህዝብ (demographic imbalance) እንዳስከተለ ወይም እንደሚያስከትል ለመጠቆም ነው።

በሌላ በኩል፣ ኤርትራ ያላት የእስር ቤት ቁጥር 380 መድረሱ ተዘግቧል። ይህም ለያንዳንዱ 1000 ሰው 1 እስር ቤት ይደርሰዋል። በቤተሰብ ደረጃ ደግሞ ለ200 ቤት አንድ እስር ቤት። ይህ መንግስት በትግሉ ዘመን ብቸኛ የነጻነት ኃይል (independence portage monopoly) በመሆን ከዚያም የመስዋእትነት ውርሻ ብቸኛ አስጠባቂ (martyrs' wish guardianship monopoly) በመሆን፣ አሁን ደግሞ ብቸኛ የጉልበትና ሴኩሪቲ ባለቤት (force and security monopoly) በመሆን፣ የራሱን ህዝብ እያስጨነቀና የመቆጣጠርያ መሳርያዎችን እየቀያየረ መደላድሉን አጠናክሯል።

የአቶ ኢሳያስ መንግስት ካልወደደህ ብዙ አጉል መበቀያ መንገዶች አሉት። ቅርብ ከተገኘህለት ቀላል ነው። ፀሃይን ለዘላለሙ መከልከል (እስር)። ራቅ ካልክ መንቀሳቀሻን መንጠቅ (ፓስፖርት፣ ዜግነት)። ቂም የተያዘበት ሰው ቅጣቱን ሳያገኝ አስቀድሞ የሞተ እንደሆነም የትም አያመልጥም። ማረፍያ ቁራሽ መሬት ይከለከላል (መቃብር)። ይህ በእርግጥ በአሁኗ ኤርትራ ተደርጓል።

አምባሳደር ሃይሌ መርቆርዮስም የታገሉላትና ያገለገሏት ኤርትራ ፓስፖርታቸውን ነጥቃ ስታባርራቸው በስተርጅና የማያውቋትና የማታውቃቸው ደቡብ አፍሪካ ማደጎ ተቀበለቻቸው። ታዋቂ እንደመሆናቸው፣ የአምባሳደር ሃይሌ ዜግነት መነጠቅ፣ የክብርና የማንነት ፈተና ይሆን እንደሆነ እንጂ የህልውና ጉዳይ አይደለም። ለሌሎች በርካቶች ግን የህልውና ጉዳይ ነው።

### *3. ዘመነ ፍዳ- "ወንድምህ የት ነው?"*

"ወንድምህ የት ነው?" ይህ ጥያቄ በኤርትራ የካቶሊካዊት ቤተክርስትያን አራት ካህናት አባቶች በበተኑት 28 ገጽ ባካተተ ጽሁፍ ላይ የሰዎች ህሊና በሚኮረኩር መልኩ ያነሱት ጥያቄ ነው። አበቶቹ ይህን ቃል ከበተኑ በኋላ እንኳ ሁለት ዓመት ሆነው። ከዚያ ወዲህም ግን ብዙ ወንድሞች ጠፍተዋል። ጥያቄውን አንስቶ ወንድሙን ፍለጋ የተንቀሳቀሰ እምብዛም ነው። 'እየየም ሲደላ ነው' ነውና ለምን አልሆነም ብለን በኤርትራውያን ላይ መፍረድ አይቻለንም። ማድረግ እምንችለው የወንድምነታችን መወጣት ነው።

በአሁኑ ወቅት ከለላ-ጠለላ አጥተው በከፋ ስቃይና መንከራተት ያሉ ኤርትራውያን በመቶዎች ሺዎች ይገመታሉ። ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ኤርትራውያን ቁጥር ከጊዜ ጋር እየጨመረ ነው። ቆይቶ ይቀንሳል የሚያሰኝ ነገር አይታይም። በቅርቡ አስመራ በጠራራ ጸሃይ ወላጆች ፊት ወጣቶች በጥይት ተደብድበዋል። ወጣቶቹ በግድ ታፍሰው አሰብ አካባቢ ወደሚገኘው ወታደራዊ ማሰልጠኛ ሲወሰዱ አምልጠው ለመሄድ ሲሞክሩ ለመግደል-ብቻ-ተኩስ የሚል መመርያ በተሰጣቸው የጸጥታ ሰዎች ነበር የተገደሉት። ድርጊቱ በየድንበሩ አካባቢ፣ በሲናይ በረሃዎችና በሜድትራንያን ባህር ራቅ ብለው የቆዩትን የኤርትራ የመቅዘፍት ቀጠናዎች ወደ መዲናይቷም መዝለቃቸው አመላካች ነው።

የኤርትራ ወጣት ሞት በረገጠው ኮቴ ላይ እየተራመደ የሚጓዝ ይመስላል።

ከአረመኔዎቹ በደዊኖች በተአምር ተርፈው ወደ እስራኤል የዘለቁ ኤርትራውያን በሚያሳፍር ነውረኛ ውሳኔ ወደ ሩዋንዳና ኡጋንዳ እየተላለፉ መሆናቸው ሚድያዎች ዘግበዋል። ሮዋንዳና ኡጋንዳ ኤርትራውያን ስደተኞችን ከእስራኤል ሲረከቡ በርከት ያለ ጦር መሳርያ ወረታ ተከፍለዋቸው ነው።

እንግሊዝና የአውሮጳ ህብረት አባል አገራት ስደተኞች ለመቀነስ በሚል ስሌት የኤርትራ ወጣቶች ስደት የኢኮኖሚና የኑሮ ሁኔታዎች የፈጠሩት ችግር እንደሆነ የማይታመኑ ጭብጦች በመጥቀስ አቋሙን ካሸጋሸገ በኋላ የስራና የትምህርት ዕድሎች ለመክፈት በሚል የትብብር ማዕቀፍ 200 ሚልዮን ዩሮ ለኤርትራ መንግስት ድጎማ ለመስጠት ፈረመ። ነገር ግን የስደት-ፍልሰት ምክንያቱ መግቢያ እንጂ መውጪያ የሌለው 'የውትድርናና ነጻ አገልግሎት ስርዓቱ ነው' የሚል ትክክለኛ አገላለጽ በሰፊው ተሰራጭቶ ስለቆየ፣ የአውሮፓ ህብረት መሪዎች የኤርትራ መንግስት ይህን ፖሊሲ ወደ መደበኛ ገደቡ፣ ወደ 18 ወራት እንዲመልሰውና እስከአሁን የነበሩትን እንዲያሰናብት ሲጠይቅ የኤርትራ መንግስት አላንገራገረም [2]።

ከዚያ በኋላ የኤርትራ መንግስት ሰልጣኞቹንና ነጻ አገልጋዮቹን ለማቆየት የተጠቀመበት የማታለያ ዘዴ ከፍተኛ የደመወዝ ጭማሪ እንዳደረገ ውስጥ ለውስጥ በማስወራት [3]፣ እንዲሁም ቆየት ብለው ራሳቸው ፕረዚዳንቱ በይፋ እንዲያረጋግጡት በማድረግ "አስናብቱን" የሚል ጥያቄ እንዳይመጣ እንደ አንድ አማላይ ማቆያ ተጠቀመበት[4]። ይህም ሆኖ ግን ወጣቱ ነጻ ምርጫው መሰናበት እንጂ መቆየት እንዳልሆነ ግልጽ ሆነ።

የአቶ ኢሳያስ መንግስት ለዓለምና ለአውሮፓ መሪዎች የሰጠውን የውትድርናና ነጻ አገራዊ አገልግሎት ዘመን ገደብ የማክበር ቃል ለማጠፍ ትንሽ ድራማ መፍጠር ነበረበት። መጀመርያ በሰሜናዊ ምዕራብ ጫፍ በግል ወርቅ ለቀማ የነበሩትን ከ40-80 የሚሆኑትን ኢትዮጵያውያን አስገድዶ አፍኖ ወደ ኤርትራ ያሻግራል[5]። የኢትዮጵያ መንግስት እንደወትሮው ሁሉ አጸፋዊና ተመጣጣኝ እርምጃ እወስዳለሁ ሲል አቋሙን ይፋ ያደርጋል[6]። ከዚያም እንደ ኢሳት ባሉ ተባባሪ ሚድያዎች "ግዙፍ ወታደራዊ ንቅናቄ ከኢትዮጵያ ወደ ድንበር አቅጣጫ" እየተደረገ እንደሆነ በሰበር ዜናዎችና ትንታኔዎች ይስተጋባል [7]። ከዚያ በአቶ የማነ ገብረመስቀል በኩል "በቅን ልቦና ወደ 18 ወራት ልንቀንሰው አስበን ነበር። ኢትዮጵያ ልትወረን እየተንቀሳቀሰችና እያስፈራራች ባለችበት ወቅት አገራዊ የውትድርናና የነጻ አገልግሎት ዘመቻው ያለ ገደብ ከማስቀጠል ምንም ምርጫ የለንም"[8] የሚል አዋጅ ያስነግራል።

## 4. *የኢሳያስ ስልጣን*

ስልጣን የሚገኘው በብዙ መንገድ ነው። ከዜጎች ይሁንታ፣ ዕውቀና ከተጎናጸፈ ልዩ ችሎታ፣ በስኬትና ውጤት፣ በማስመሰልና ሸር ከሚገኝ ድጋፍ፣ እንዲሁም ከለየለት ኃይልና ድፍጠጣ ወዘተ። አቶ ኢሳያስ በነኝህ ሁሉ አልፈው መጨረሻ ላይ በተጠቀሰው ክልል ላይ ያሉ ይመስላል። በዚህ ሁሉ ግን የአካሄዱ መልክ ቢለዋወጥ ፍላጎታቸውና ምኞታቸው ሳይቀያየር ዘልቋል። እዚህ ዝርዝር ውስጥ መግባት ያስፈለገው፣ የኤርትራ መንግስት ሁሌም ታክቲክ ይቀይራል እንጂ አቋምና ፖሊሲ ቀይሮ አያውቅም የሚለውን ነጥብ ለማስረገጥ ነው። አቋምና ፖሊሲ የሚቀይረው ምናልባት ለአጭር ጊዜና ከህልውናው ጋር የተያያዘ ተግዳሮት ሲገጥመው ብቻ ነው። የአቶ ኢሳያስ መንግስት ትክክለኛ ባህርይ ማወቅ ማለት "ጊዜና ተሞክሮ መሻሻል ያመጣሉ" ከሚል ተጨባጭ ያልሆነ ተስፋና ጥበቃ ያላቅቃል።

የኤርትራ መንግስት ሁለት ዓላማ ይዞ ተነሳ። በአገሩ ውስጥ ፍጹም የፖለቲካ ሞኖፖል ማረጋገጥና በአፍሪካ ቀንድ ደግሞ የጎበዝ አለቃ መሆን። ሁለቱ ዓላማዎች እስካሁን የሙጥኝ እንዳላቸው አለ። ሁለቱንም ለማሳካት ማንኛውም ስልትና ሃብት ይጠቀማል። እነዚህ ሁለት ነገሮች ለመሆን ያለው ተጨባጭ አቅም ምኞቱን ለማስፈጸም የሚያበቃ ቢሆንም ባይሆንም፣ አቶ ኢሳያስ እስካሉ ድረስ ዓላማዎቹ ይቀጥላሉ። እነሱን ለማሳካት ሲባልም ኤርትራና ኤርትራዊ ማንኛውም ዋጋ ሊከፍል ግድ ነው። ለምሳሌ ስደቱ የዚያ ዋጋ አካል ነው።

ተማረው የሚሰደዱ ወጣቶች በትክክል የስርዓቱ ተቃዋሚ ለመሆን ቅርብ ዝንባሌ ላይ እንደሆኑ የሚገመቱ ናቸው። ስለዚህ አገር ቤት ከሚቆዩ ይልቅ በስደት ቢበታተኑ ስጋት ከመቀነስ አንጻር ለአቶ ኢሳያስ መንግስት ተመራጩ ሁኔታ ሆኖ ይታያል። አገር ለቀው ከወጡ በኋላ የስደት ካምፕ ውስጥ ሆነው ስለ አቶ ኢሳያስ ስርዓት ባህርይና ትግል ለማውጠንጠን የሚኖራቸው ተነሳሽነት ዝቅ ያለ ነው። የአቶ ኢስያስ መንግስትም ይህን እውነታ በትክክል ይገነዘባል። ያም ሆኖ ስርዓቱ የኤርትራ ወጣቶች እዚህ በቅርብ ኢትዮጵያ ከሚቆዩ አርቀው ቢሄዱ የተቃውሞ ስጋቱም ያን ያህል ስለሚርቅ የስርዓቱ ምርጫ እንደሚሆን ይታመናል። ወደ ሶስተኛ አገር ቢሻገሩም ቀሪ ቤተሰቦቻቸው በነሱ መውጣት ምክንያት የሚቀጡት 50ሺ ናቅፋ፣ መንገድ ለሚያሻግሯቸው ሰዎች፣ ለመጓጓዣና ለስንቅና ለመሳሰሉ የተለያዩ ዕዳዎች ተጋልጠው ስለሚወጡ ተደራራቢ ሰራ ለመስራት እንጂ በተቃውሞ ትግል ውስጥ ለመሳተፍ የሚኖራቸው ስሜትና ዝግጁነት ኢምንት ነው። ይህን መሰል ሁኔታ፣ ተቃውሞ ለመቀነስና ሬሚታንስም ለመጨመር የአቶ ኢሳያስ መንግስት ፍላጎት እንደሚሆን ይታወቃል።

የአቶ ኢሳያስ መንገድ ግልጽ ነው። በጊዜ ሂደት ይሻሻላል የሚል ተስፋ መያዝ ልክ እንደማይሆን አይተናል። የኤርትራውያን መከራና ስደትም ይጨምር እንደሆን እንጂ እንደማይቀንስ በቂ ማሳያና አስረጅ አለ። በዚያውም ልክ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ስጋት ቀለል ይላል። የአውሮፓ ሃገሮች “የስደተኞች ቁጥር እንቀንስ” የሚል አቋማቸው እያጠናከሩ የሚገፉበት ይመስላል። የእስራኤል ውሳኔ ትንሽ ከረር ያለ ነው። ጭራሽ የገቡትንም የኤርትራ ስደተኞች ወደ አፍሪካ አገር በመመለስ ላይ ናት።

የኤርትራ ህዝብ ሙሉ በሙሉ በአቶ ኢሳያስ ሙሉ ቁጥጥር ገብቷል። ኢትዮጵያን በማወክ ወይም በማዳከም፣ ሌሎች የአፍሪካ ሃገሮችን በተጽእኖ ስር አስገብቶ የአካባቢው የማያሻማ የጎበዝ አለቅነት ብትር በመጨበጥ የዓረብ ቱጃሮችንና የምዕራብ ኃያላንን ትኩረት ማግኘት ይቻላል የሚለው የትናንት ህልማቸው ዛሬም አለ፣ ነገም ይኖራል። እዚህ ላይ ያንን ለማድረግ የሚያስችል አቅም ‘አላቸው የላቸውም የሚለው ክርክር አይደለም ዋናው ቁምነገር። እሳቸው ጋር ያለው ስሜትና ምኞት ነው። ጦርነቱን የማሸነፍ አቅም ሳይኖራቸው ጦርነት ጀምረዋል። ማዕቀብና መገለል የሚያስከትለውን የሶማሊያ አሸባሪዎችን የመደገፍና የማሰልጠን ምርጫ ወስደዋል። ስለዚህ የፕረዚዳንት ኢሳያስ ስሜትና ምኞት እንደ ተጨባጭ ሁኔታና መነሻ መገንዘቡ ይጠቅማል። እንጂ ውጤቱን እየገመቱና እያሰሉ ይቆጠባሉ የሚለው ስሌት ያሳስታል። ቅድም እንዳልነው፣ እሳቸው ስለውጤቱ የሚጨነቁት በቀጥታና በቅርብ ከህልውናቸው ጋር የሚያይዘው ነገር እንዳለ ብቻ ነው።

የአቶ ኢሳያስ መንግስት ምህዋረ ፖለቲካው የሚሽከረከረው “በኢትዮጵያ ውድቀት የህዝባዊ ግንባር ትንሳኤና ዝና ተመልሶ ይመጣል” በሚል የአስተሳሰብ ኦርቢት ዙርያ ነው። ይህ ዝም ብሎ እንደ አጠቃላይ አባባል ለማለት ያህል ብቻ ተብሎ የሚታለፍ ነጥብ አይደለም። እሳቸው ሁለመናቸው የሰጡበት፣ ሁሉም ዓይነት ሃብት ለዚህ ፕሮጀክት መድበው፣ ዝርዝር ዕቅድ ነድፈው ሌተቀን የሚሰሩበት ቁልፍ መርሃ ግብራቸው ሆኖ ጎልቶ የወጣ ነው። አሁን ብቸኛው አማራጭ ብለው የሚረባረቡበት ፕሮጀክት ሆነ እንጂ አዲስ ዝንባሌ አይደለም፤ የነበረና የዘለቀ ነው።

ዛሬ እምናየው ትላንት ያየነውን ነው። ነገም እምናየው ዛሬ ያየነውን ነው። ሁኔታዎች እንደዚህ መሆናቸው መልካም ነገርም አለው። ብዙ የተለወጠ የዓላምዎችና አሰላለፎች ሽግሽግ ሁኔታ ባለመኖሩ ትላንት ሊያገለግለን ይችል የነበረው መፍትሄ፣ ዛሬም ነገም ይሰራል። መፍትሄውም አቶ ኢስያስና መንግስታቸው ላይ፣ ወይም ኤርትራ ላይ ከማተኮር ይልቅ ኤርትራውያን ላይ በማተኮር የሚገኝ ነው።

## *5. ኢትዮጵያ ችግር ላይ ላሉት ኤርትራውያን የተሻለ ማድረግ አትችልምን?*

ኤርትራውያን በገፍ አገራቸውን እየተው ሲመጡ እየተቀበሉ ካምፕ ውስጥ ማስቀመጥ ሳይሆን ወደ አገራቸው የመጡ ያህል ሆኖ እንዲሰማቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ የመፍትሄው መጀመርያ ነው። ከፖለቲካ አንጻር ካየነው እጅግ ብዙ ዘላቂ ስትራተጂክ ጠቀሜታ አለው። ከሰብአዊነትና ሞራል አንጻርም ሊደረግ የሚገባው ነገር ነው።

ለነዚህ ኤርትራውያን፣ ከኤርትራ ቀጥላ የምትኖራቸው የቀረበች አገር ኢትዮጵያ ካልሆነች የቷ ናት? ለመሆኑ አንድ ኤርትራዊ የሌላ አገር ዜግነት መውሰድ ቢፈልግ፣ አለያም በሁኔታዎች ቢገደድ፣ ይህን ዜግነት የማግኘት ዕድል ለመስጠት የመጀመርያዋ አገር መሆን ያለባት የትኛዋ ናት? ደቡብ አፍሪካ ወይስ ኢትዮጵያ? አሜሪካና ካናዳ ወይስ ኢትዮጵያ? እንግሊዝና ስዌደን ወይስ ኢትዮጵያ?

አሜሪካ ስደተኞችን ተቀብላ ማቋቋምና ማስለመድ ስትፈጥር ጀምሮ እስከ አሁን በስፋት ታካሂዳለች። ማስለመዱ እስከ አሜሪካዊ ዜግነት ማጉናጸፍ የሚሄድ ነው። የካናዳ ፖሊስም ተመሳሳይ ነው። ብዙዎቹ የአውሮፓ አገሮች፣ እንዲሁም አውስትራሊያ ስደተኞችን፣ በመቀበል፣ በማቋቋምና በማስለመድ ይታወቃሉ። ይሞገሳሉ። ይህ ፖሊሲ ሲጠቅማቸው እንጂ ሲጎዳቸው አይታይም።

ሁሉም አገሮች እንደስደተኞች መዳራሽነታቸው የፖሊሲዎቻቸው አቅጣጫ በአንድ በኩል ምርጥ ክህሎትና ብቃት ያላቸው ሙያተኞች/ምሁራን ወይም የፈጠራ ሰዎች ወዘት ለማስኮብለል፣ በሌላ በኩል መጠጊያ አጥተው ለተቸገሩት የሌላ አገር ዜጎች ጠለላ-ከለላ ለመሆን በብልጠትና በሰብአዊነት የተቃኙ ናቸው።

እነዚህ አገሮች የሌላ አገር ዜጎች ስደተኞችን በመቀበል፣ በማስተናገድ፣ በማቋቋምና በማስለመድ ዙርያ ያሉዋቸውን ህጎችና ደንቦች አንዴ ወጥተው በዛው ተቸክለው የቀሩ አይደሉም። በየጊዜው የሚሻሻሉና ሁኔታዎችን ለመመጠን እየሰፉና እየጠበቡ ከሁኔታዎች፣ ከክስተቶች እንዲሁም ተቀባይ አገሮቹ ካላቸው ዝግጁነትና ቀዳሚ ትኩረት ጋር እየተጣጣሙ እንዲዘልቁ ታስበው የተቀረጹ ናቸው።

ሶርያና የመን ችግር ላይ ያሉ አገሮች ናቸው። ዜጎቻቸው በሚያሳዝን ሁኔታ በአራቱም አቅጣጫ የትም ህይወታቸውን ለማትረፍ እግራቸው ወደ መራቸው የሚሄዱበት፣ በየመንገዱ ህይወት እስከማሳጣት ለሚያደርሱ አደጋዎች የሚጋለጡበት ትራጀዲ ይደጋገማል። በዙርያቸው ያሉ ባለነዳጅ ሃብታም አገሮች ሶርያንና የመንን ለማውደም እንጂ የመናውያንና ሶርያውያንን በዚህ ቀውጢ ጊዜ ለመታደግ አንዳችም ትብብር አላሳዩም። ብዙም የተትረፈረፈ ዓቅም የሌላት ዮርዳኖስ ናት ከነዚህ ስደተኞች የተወሰኑትን ተቀብላ ለማቋቋም ውሱን ተነሳሽነትና ተግባር ያሳየችው። ዮርዳኖስ ከዚህ በፊትም ዒራቅ ጦርነት ውስጥ በነበረችበት ጊዜ፣ ቀደም ብሎም ለተቸገሩ ፍልስጤማውያን ተመሳሳይ በጎ አቋም ማሳየቷ ይታወሳል።

በስፋትም ባይሆን፣ በአካባቢያችንም በዚህ ዓይነት በጎ ተግባር የምትጠቀስ ታንዛንያ ናት። ታንዛንያ የሁቱ ቱትሲ ግጭትና መተላለቅ በተከሰተ ጊዜ ሸሽት ላይ የነበሩትን ብቻ ሳይሆን እጇን ረዘም አድርጋ በመዘርጋት አደጋ ላይ የነበሩትን ሰዎች ወደ አገሯ እንዲሻገሩ የብሩንዲና የርዋንዳ ዜጎችን እጇን ዘርግታ ተቀብላለች፣ አቋቁማለች፣ አስለምዳለች። ይህ የተቸገሩ ስደተኞች በራሳቸው ውሳኔ ድንበር ጥሰው ከመጡ በኋላ እንደ ቋሚ ስደተኛ ካምፕ ውስጥ እንዲጠለሉ ወይም እንዲኖሩ ከማድረግ ጋር ትልቅ ልዩነት አለው።

የደግነት ትሩፋት የሚበልጠው ለራስ ነው። የንፍገት ክፋት ግን በሌሎች ላይ ነው።

ኤርትራውያን ከኢትዮጵያዊ ዜግነት የወጡበት ሁኔታ ፖለቲካዊ መልክ ይዞ ጀምሮ ወደ ህጋዊነት የተሸጋገረ ነው። እንጂማ ከመረብ ወዲህና ወዲያ ያሉ የትግርኛ ተናጋሪዎች፣ የኩናማ ነገዶች፣ መነኹሴቶና ኢሮብ፣ ይህኛውና ያኛው ዓፋር የተለያዩ የመሆናቸው ጉዳይ ከፖለቲካ ውጭ የሚቀርብ አመክንዮ ፈጽሞ አይኖርም። ከፖለቲካ በላይ የሚታዩና የገዘፉ ሌሎች ዕውነታዎች ግን አሉ። አንደኛ፣ አንድና ወንድም-እህት ህዝብ መሆኑ ነው። ሁለተኛ፣ በልዩነት ከኖረው ዘመን በአንድነት የኖረው ዘመን እጅግ ይበልጣል፣ ይረዝማል። ሶስተኛ፣ በፖለቲካ ምክንያት የተከተለው ህጋዊ መለያየት አለመረዳዳት፣ አለመደጋገፍንና የመለያየት ምርጫውን ፈጽሞ ዳግም አለማጤን፣ ወይም የመለያየቱ ፋይዳና ቀጣይነት በይደር ይዞ ከዛ መለስ ያሉ ዝምድናዎችን አለማደስ ማለት ሊሆን አይችልም። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ኤርትራውያን፣ በከተሞችም በስደተኛ ካምፖችም ያሉት ኤርትራውያን የኢትዮጵያ ዜግነት የሚያገኙበት የተፋጠነ ህግና አሰራር፣ Speedy Renaturalization Policy and Process ቢወጣ ተገቢም ጠቃሚም ነው።

ይህን በማድረግ የሚመጣ ጉዳት የለም ወይም የሌለ ያህል የሚቆጠር ነው፣ ከጉዳቱ ፋይዳው ይበልጣል። በተለይም ከረዥም ጊዜና ከስትራተጂክ አገራዊ ጥቅም አንጻር።

ለኤርትራውያን ደግሞ ምርጫ የመስጠት ያህል ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ኤርትራ የጎረበጠችባቸው ኤርትራውያን ቀጣይ ምርጫቸው ኢትዮጵያ መሆን ያለበት ይመስለኛል። ለኤርትራዊነት ከኢትዮጵያዊነት በላይ የቀረበ ዝምድና የለም። ይሁንና ይህ ሲፈልጉት ብቻ የሚወስዱት ስለሆነ ሁሉም ባይመርጡት ጥቂቶቹ፣ አሁን ባይመርጡት ወደፊት እንደ አማራጭ ዕድል ስለሚያዩት ኪሳራ ይዞ የመጣ ምርጫ አይሆንም። እንደውም አንዳንዶቹ በጥርጣሬ መልክ ሲያነሱት የሚደመጠው መሬት ወይም ወደብ ፍለጋ ከሚባለው የተላቀቀና በአሁን ጊዜ እጅግ አፋኝ በሆነ ስርዓት መከራውን እያየ ያለውን የኤርትራ ፍልሰተኛና ውጭ ነዋሪ ምርጫ ለመስጠት በማሰብ የሚወጣ ፖሊሲ መሆኑን ከመረዳት በጥሩ መንፈስ ይቀበሉታል ተብሎ ይገመታል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ድሮም እንደራሱ ስለሚያያቸው ለዚህ ዓይነት ፖሊሲ ድጋፍ እንጂ ተቃውሞ ይኖረዋል ተብሎ አይጠበቅም። በዚህ መልክ ኢትዮጵያውያን የዚህ ዓይነት እርምጃ የሚያዩት ተለይቶ ሰንብቶ እንደገና ወደቤተሰቡ እንደሚቀላቀል የቤተሰብ አባል በደስታ እንደሚሆን ለመጠራጠር የሚያስችል ምክንያት የለም። ደግሞስ ሲሄዱ እንኳ በደግነት የሸኘ ህዝብ በሚመለስ ሰው ደስተኛ ላይሆን አይችልም።

የኢትዮጵያ መንግስት በስደት መልክም ቢሆን ለኤርትራውያን እስከአሁን የሰጠው ድጋፍ ኢትዮጵያውያን ያዩት በአዎንታ ነው። በጦርነቱ ጊዜ ተባርረው ለነበሩ ኤርትራውያን ተመልሰው ንብረታቸው እንዲረከቡ ከፈለጉም ያኔ የነበራቸውን ቢዝነስ እንዲቀጥሉ የሚፈቅድ መመርያ በማውጣቱ ኢትዮጵያውያን የተቀበሉት በደስታ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ለኤርትራውያን ወጣቶች የትምህርት ዕድል ለመስጠት ዓቅሙ የፈቀደለትን በማድረጉ የተከፋ ኢትዮጵያዊ አላውቅም።

የዓለም ማህበረሰብና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ይህ ቢደረግ በአድናቆት የሚያዩት እንደሚሆን ጥያቄ የለውም። እንኳንና ለዚህ ከፍ ላለ በጎ እርምጃ ቀርቶ በነበረውም ሁኔታ ኢትዮጵያ ለጎረቤት አገር ሰደተኞች በምታሳየው ቀና ትብብርና ፈቃደኝነት ሁሌም ተመስጋኝ ናት። ይህ እርምጃ ቢጨመር ኢትዮጵያ የበለጠ በጎ ገጽታዋን ታሳይበታለች።

## *6. ህጉ*

ባነሳነው ጭብጥ ዙርያ ህጉ ምን እንደሚል ቀጠለን እናየዋለን። ነገር ግን ህጉን መደፍጠጥና ማፍረስ ነው እንጂ እማንችለው በህጋዊ መንገድ ሊስተካከል የሚችል ነው። ዋናው ጉዳይ ቢቻል ባለው የህግ ማዕቀፍ፣ ካልሆነም የህግ ማስተካከያ በማድረግ ሊሰራ የሚገባ አሳማኝ ቁምነገር "አለ ወይስ የለም" የሚለውን መመርመሩ ነው። የተነሳው ጉዳይ ከሰብአዊነትም፣ ከኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅምም አንጻር በኢትዮጵያ ከተሞችና በሰደተኛ ካምፖች ውስጥ ያሉትን ኤርትራውያን በፍቃደኝነት ዜግነት (naturalization process) የሚጎናጸፉበትን የተፋጠነ ሂደት ቢቀየስ መልካም ነው የሚል የፖሊሲ ሃሳብ ነው።

የኢትዮጵያ ህገ መንግስትም፣ በ2003 የወጣ የዜግነት አዋጅ ቁጥር 378/2003 በኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ዜግነት ማግኘት ወይም መጎናጸፍ የሚቻለው በመወለድ ወይም በህጋዊ መንገድ በማለፍ ነው ሲሉ ይደነግጋሉ። በመወለድ ሲባል ከአንድ ወይም ከሁለት ኢትዮጵያን ወላጆች በመወለድ የሚለው ሁሉም አገሮች ላይ ያለ የአብዛኛው ዜጋ መንገድ ነው። በዚሁ "በመወለድ" በሚለው ጽንሰ ሃሳብ ስር "በኢትዮጵያ ምድር ያለወላጅና ያለሌላ የታወቀ ዜግነት የተገኘ ማንኛውም ህጻን ከኢትዮጵያ ወላጆች እንደተገኘ ይቆጠራል" የሚል ድንጋጌ ተካቷል።

እዚህኛው ህግ ውስጥም ቢሆን፣ በትውልድ የሚለውንም ቢሆን አሁን እየተወያየንበት ያለውን ጉዳይ በተመለከተ የሚያወያይ ነጥብ አይጠፋም። ብዙ ኢትዮጵያውያንና አሁን-ኤርትራያን ተጋብተው በርካታ ልጆች እንዳፈሩ ይታወቃል። እናም አንድ ወላጆች ከኤርትራ በመሆኑ ብቻ በልዩ ልዩ ግፊቶች አልያም በራሳቸው ምርጫ የኤርትራ ዜግነት የወሰዱ ይኖራሉ። እነዚህ ወገኖች አሁን ዕድሉ ቢያገኙ፣ የኤርትራን ዜግነት መልሰው የኢትዮጵያውን ዜግነት እንዲሰጣቸው ይህን "አንዱ ወላጅ ኢትዮጵያዊ ከሆነ የትውልድ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ይኖሯል" የሚለውን ህግ ለመጠቀም እንዳይችሉ የሚከለክል ሁኔታ እንዳለ ለኔ ግልጽ አይደለም።

የዚህ ህግ አንቀጽ 22፣ በአንድ ወቅት ኢትዮጵያውያን የነበሩ ዜጎች፣ ሌላ ዜግነት ከወሰዱ በኋላ እንደገና ወደ ኢትዮጵያዊነት መመለስ ቢፈልጉ ስለሚስተናገዱበት ህግና ስነስርዓት ይዘረዝራል። ለማስታወስ ያህል፣ ኢትዮጵያዊ ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደ፣ የተወለደው ከአንድ ወይም ከሁለቱ ኢትዮጵያዊ ወላጆች ሲሆንና ሌላ ዜግነት ያልወሰደ ነው። በአንቀጽ 22 መሰረት እንግዲህ ቀደም ብሎ ኢትዮጵያዊ የነበረና ሌላ ዜግነት የወሰደ ሰው ተመልሶ ኢትዮጵያዊ መሆን ቢፈልግ የሚጠየቀው ወይም እንዲያሟላ የሚፈለገው ሁኔታ ግልጽና ቀላል ነው። ወደ ኢትዮጵያ ምድር ተመልሶ መኖር መጀመር፣ ሌላ ዜግነት መተውና ማመልከት ብቻ ናቸው።

አንቀጽ 22ን አፍታትተን እንይ። ከሪፈረንደም በፊት (በፈረንጅ 1993 ወይም ከኛ 1985 በፊት) የተወለዱ ኤርትራውያን በሙሉ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። እነዚህ ወገኖት አሁን ስደተኞች ካምፕ ውስጥም ሆነው ወይም በነዋሪነት ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ፣የኢትዮጵያ ዜግነት ለመውስድ የሚቀራቸው ስራ ማመለክት ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ኤርትራውያን በሙሉ ይህን ህግ እንዲያውቁትና እንዲጠቀሙበት ቢደረግ ብዙዎቹን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ኤርትራውያን ተጨማሪ ህግ ሳይስፈልግ በዚህ ድንጋጌ ሊስተናገዱ ይችላሉ።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ከ1985 በኋላ ተወልደው በልዩ ልዩ ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ኤርትራውያን ከቅርበት፣ ከታሪክ፣ ከሰብአዊነትና የኢትዮጵያን ጥቅም ከማረጋገጥ አኳያ የተፋጠነ ናቹራላይዜሽን ሂደት ውስጥ እንዲገቡ የሚያስችል አሰራርና ቢቀየስ መልካም ነው።

በሁለተኛው አማራጭ ማለትም በህጋዊ ሂደትና ስርዓት በማለፍ  ስለሚገኘው ዜግነት የሚደነግገውን በአዋጁ አንቀጾች ከ 5 እስከ 12 ዓንቀጾች በሰፈሩት ድንጋጌዎች የተቸገሩና አማራጩን የሚፈልጉት ኤርትራውያንን በፍጥነትና በጅምላ ሊስጥ ስለሚችል የዜግነት ወይም ናቹራላይዜሽን ስርዓት ማስተናገድ ይቻል እንደሆነ አለዚያም ለዚህ ልዩ ሁኔታ የተወሰነ የህግና የፖሊሲ ማስተካከያ ማድረግ ይጠይቅ እንደሆነና ማድረጉ ይጠቅማል ወይስ ይጎዳል የሚለውን ነጥብ አንስቶ ለመወያየትና ለመመንጎት ነው።  ህጎች የሚወጡት ለተለያየ ዓላማ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ የዜጎችንና የህዝብ መብት፣ ፍትህ፣ ደህነንትና ጥቅም በማስከበር የሃገር ህልውና ክብር ለማረጋገጥ ተብለው ነው። ለዚህ ሲባል ህጎችም ቢሆኑ በህግ ይሻራሉ፣ ይሻሻላሉ፣ ይተካሉ። ከዚህ በፊት ኢትዮጵያውያን የነበሩት አሁን ኤርትራውያን የሆኑት የቆዩትን ህጎችና አስተሳሰቦች በመለወጥ ነው።

ከሁለቱም ወገን የኢትዮጵያውያንና የኤርትራውያን መቀራረብ፣ መተባበርና መወሃድ የማይመኝ ብዙ አይደለም። የአብዛኛው ስጋት የከዚህ በፊት ስህተቶች እንዳይፈጠሩ ነው። ተገቢ ስጋት ነው። መነሻም አለው። ስህተቶቹ ወደ ተጠራቀመ ቅሬታ፣ ከዚያም ወደ ህውከት፣ ከዚያም ወደ ደም መፋሰስ የሚመሩ እንዳይሆኑ ያለፍንበትን የመከራ ታሪክ ከማስታወስ የሚነሳ ስጋት ነው። ነገር ግን የከዚህ በፊቶቹ አንድም ይሁንታ ላይ ያላተኮሩና የጉልበት አማራጭ እንደዋነኛ ማስፈጸምያ መሳርያ፣ አሊያም ከሰው ይልቅ መሬትና ግዛት ላይ ይበልጥ ያተኮሩ ስለነበሩ ይመስለኛል ስህተት እሚሆኑት። ሰብአዊነት ላይ እንዲሁም ሰውና ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ ከግዛት ማስፋፍትና ጉልበት የጸዱ በጎ ማስተሳሰርያዎች እያበጁ መሄድ ግን የስጋት ምንጭ ሳይሆን የስጋት ማስወጋጃና የህዝቦች ንጹህ ዝምድና ለመገንባት የሚያገለግል መደላድል ማሰናዳት ማለት ነው።

ወደድንም ጠላንም የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች በመካከላቸው በፍጥነት እየወፈረና እየረዘመ የሚሄድ ስውር ግን በአራት እጥፍ የወፈረና የረዘመ የበርሊን ግንብ እየተገነባበት ይገኛል። የመጀምርያው ግንብ ፖለቲካዊ ብቻ ይመስል ነበር። ቀጥሎ በጦርነቱ ምክንያት የኢኮኖሚውም ንግዱም ግንኙነት ክር የሚበጥስ ግንብ ተጨመረበት። በተቀራውም የግንኙነት ክሮቹ እየበጣጠሱ፣ የልዩነት ግንቡን እሚያጠናክሩ፣ በእርቅ ቦታ መራራቅን የሚሰብኩ፣ የአሁኑን የወድፊቱን ዕድሎች ብቻ ሳይሆን ያለፈውንም የግንኙነት ታሪኩን የሚቆራርጡ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳዎች ያለማቋረጥ በጎ ቅርርቦችን በመበከል ላይ ተጠምደዋል። በዚህም ምክንያት የባህልና የታሪክ ልዩነት ግንቦችም በተደራቢነት እየተገነቡ ይሄዳሉ። በዚህ ምክንያት ከ40 በታች ያሉ ኤርትራ ውስጥ ያሉ ኤርትራውያውያን ያደጉት ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ክፉ ክፉውንካልሆነ ምንም በጎ ነገር ሳይሰሙ ነው። እነዚህ ከጠቅላላው የኤርትራ ህዝብ 60% እና 70%  ያላነሰ የቁጥር ድርሻ የሚሸፍኑ ናቸው። ትንሽ ቆይቶ ሙሉውን ህዝብ ማለት ነው።

ይህ በዕቅድ እንጂ ባጋጣሚ የመጣ አይደለም። ለዚህ ነው በጦርነቱ ወቅት ፕረዚዳንት ኢሳያስ ለኢንተርቪው ቀርበው የVOAው ስኮት ስተርንስ "ምንድነው ይህ ሁሉ የተካረረ ጸብ፣ ቅርብ ቤተሰብ ናቹህ እኮ ነው እምንሰማው" ብሎ ሲጠይቃቸው፣ "እኛና እነሱ መረብ ወንዝ ከሚለየን በላይ ታሪክ ይለየናል። እናንተ (የውጭ ሰዎች ለማለት) በየዋህነት እምታወሩት ነው። የምታውቁን ይመስላቹሃል እንጂ በጭራሽ አታውቁንም" ሲሉ በአንክሮ የተናገሩት።  ይህን አድገኛ አቅጣጫ ለመለወጥ ተጨባጭ ስራዎች አሁን ሳይሆን ትላንት መሰራት ነበረባቸው። ነገ ግን ፈጽሞ የዘገየ ነው። ይህ አሁን በዚህ ማስታወሻ እየቀረበ ያለው ሃሳብ አንዱ ዓላማም ይህን ለማስገንዘብ ነው።

## *7. ማጠቃለያ*

በትክክለኛው ጊዜ የተሰጠ ደግነት ከሚሰጠው ጥቅም በላይ በተሳሳተ ጊዜ የተነፈገ ደግነት የሚተወው ጎጂ ስሜት ብዙ ይገናል። ይህ እውነታ ጎልቶ እሚታየው ደግሞ በሰጪው እና ተቀባዩ መካከል መተሳሰብና ደግነት ይኖር ዘንድ ገዢ ግምት ሆኖ የቆየ እንደሆነ ነው። በሁለቱ መሃከል መቃቃርና መነካካት ዋናው መገለጫ ሆኖ ከቆየ ግን በዚያ ሁኔታ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚሸጋገር ትንሽዬ በጎ ጠብታ እንኳን ጎልታ ትወጣለች። ፍቅርና መደጋገፍ የሆኑትን ያህል ጸብና ቅራኔም የቅርበትና የዝምድና እንጂ የባዕድነት መገለጫዎች አይደሉም። Conflict is relational, too እንደሚባለው ማለት ነው። ዝምድና ወይም ትሥሥር  የሁለቱ ተቃራኒ - ማለትም የባዳነትና ባዕድነት፣ ዋናው መገለጫው ደግሞ ባይተዋርነት ነው።

የኤርትራ እንደ አገር ራሷን ችላ መለየት እንደሚባለው የቅኝ ግዛት ጥያቄ ጉዳይ ወይም የህዝብ መብትና ውሳኔ ጉዳይ ስለሆነ በሚል የሚታይ አይደለም። አብረው የሚታዩ ሁለት ታሳቢ ነጥቦች አሉ። በኤርትራውያን በኩል ከመለየታቸው በፊት ከነበራቸው ኑሮና መብት ያላነሰ ይሆን ዘንድ፣ በኢትዮጵያውያን በኩል ደግሞ ከኤርትራ መልካም ጉርብትናና ሰላም። እነዚህ ታሳቢዎች በቦታው ከሌሉ የመለየቱ ፋይዳ ሁሌም በጥያቄ ምልክት ላይ ነው። የመለየቱ ፍጻሜ ወደኋላ መመለስ አይቻል ይሆናል። ነገር ግን ከመለያየቱ ጋር የግድ መኖር ያለባቸው እነዛ ሁለት እሳቤዎች ይሟሉ ዘንድ የሚያስፈልግ ስራ በሙሉ መሰራት አለበት።

በኢትዮጵያ በኩል የሙሉ ሰላምና የመልካም ጉርብትና ጥያቄ ስትራተጂክ ነው። ይህ የሚገኘው የኤርትራን የፖለቲካ ሁኔታ እንዲለወጥና እንዲሻሻል በሚያስችሉ መፍትሄዎች ላይ በመስራት ነው። መፍትሄዎቹ ከኤርትራ ህዝብ ጋር በመስራት ነው የሚገኙት። በስደት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡትም ሆነ ቀደም ብለው እዚህ የቆዩት ኤርትራውያን የሚፈለገው መፍትሄ አካል እንዲሆኑ ሁለ ገብ ስራዎች መስራት ያስፈልጋል። አንዱም በተፋጠነ ሁኔታ ማቋቋምና የዜግነት አማራጭ ዕድል ክፍት ማድረግ ከብዙዎች ስራዎች አንዱ ነው።

ኢትዮጵያ የቅርበቷ ያህል ለሚፈልጉትና ለተቸገሩ ኤርትራውያን እስከ ዜግነት መስጠት የዘለቀ የማቅረብና የመታደግ ተነሳሽነት ብትወስድ ያን ያህል ስር ነቀል ውሳኔ ወይም የተለጠጠ ደግነት ተደርጎ መታየት የለበትም። መሄድ መብት ሆኖ መመለስ እንዴት አይሆንም?! ይህ ከመሬቱ ይልቅ ሰውን የማስቀደም ትልቅና አስተዋይ ዕይታ ነው። አሁን ያለው ገዢ ፓርቲ ለኤርትራ መለየት ከበቂ በላይ ለdeintegration በመተባበር የሚታማው ያህል ፈቃደኛ የሆኑትን በርካታ ኤርትራውያን ኢትዮጵያዊነትን መልሰው እንዲጎናጸፉ በማድረግ ለreintegration ገንቢ አስተዋጽኦ በማንጠፍ ይመሰገናል። ወቅታዊ ሃላፊነቱም የሚጠይቀው ቁምነገር ነው። ተግባሩ ሞራላዊም ሰብአዊም ነው። ከዚያ በላይ ግን የኢትዮጵያ አገራዊ ስትራተጂካዊ ጥቅሞች ማስከበርያ መደላድል ለመፍጠር የሚረዳ ወሳኝ አቅጣጫ ነው።

ዳደ ደስታ ከኤርማይን ሚድያ

~/~

1. http://awate.com/politics-of-census
   I highly recommend reading this article for those interested in demographic politics of Eritrea
2. Yemane Gebreab: “We have been reforming and bringing change to that National Service program. But now, after reviewing our situation and the situation in our region as a whole, we have decided to go back to 18 months. The implementation of that policy will start on the current bunch” Yemene Gebreab

   http://www.madote.com/2015/04/yemeane-ghebreab-speaks-on-limiting.html

3. Eritrea Raising National Service Salary by 700%;

   http://www.tesfanews.net/eritrea-national-service-salaries-no-18-months-limit/

4. In the absence international will to ‘guarantee’ Eritrea’s security concerns, the immediate option for Eritrea is to make staying in the country attractive first by improving the salary of National Service conscripts by up to 700 percent.

   http://www.tesfanews.net/eritrea-national-service-salaries-no-18-months-limit/

5. Multiple sources toldSudan Tribune Saturday that a group of armed men allegedly dressed in Eritrean army uniforms crossed borders to Ethiopia and forcibly kidnapped over 80 young Ethiopian miners who were mining gold in Tigray regional state

   http://www.sudantribune.com/spip.php?article58070

6. The Ethiopian government has vowed to take what it said will be “appropriate measures” against Eritrea on the aftermath of the abduction of some 85 Ethiopians by the Red Sea State.

   http://www.thereporterethiopia.com/content/ethiopia-warns-eritrea-over-mass-abduction

7. Esat Breaking News፡ በኦሮሚያ ዓመጽ ምክንያት ውጥረት ላይ የሰነበተው የወያኔ መንግስት ባለፉት ሁለት ቀናት በርካታ ከባባድ ጦር መሳሪያዎችና ወታደሮች ወደ ኤርትራ ድንበር ላይ እያስጠጋ መሆኑ ታወቀ።

   https://www.youtube.com/watch?v=2U1ZqfmCjkA

8. Eritrea won't shorten national service despite migration fears. Yemane Gebremeskel said demobilization is dependent up on the condition of the absence of any threat from Ethiopia.

   http://www.reuters.com/article/us-eritrea-politics-insight-idUSKCN0VY0M5